# የመንግስትና የግል አጋርነት አዋጅ ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ
## ምዕራፍ አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አውጭው ባለስልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በመንግስትና የግል አጋርነት አዋጅ ቁጥር 1076/2010 አንቀጽ 65(2) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል።

2. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የመንግስትና የግል አጋርነት አዋጅ ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 55/2010 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

3. **ትርጓሜ**

በአዋጁ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላት በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ እንደሆነ ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የተለየ ትርጉም ካልተሰጣቸው በስተቀር በአዋጁ የተሰጠቸውን ትርጉም ይይዛሉ። ከዚህ በተጨማሪ በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "አዋጅ" ማለት የመንግስትና የግል አጋርነትን ለመደንገግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 1076/2010 ነው።
2. "በመንግስት የሚደረግ ድጋፍ" ማለት በአዋጁ አንቀጽ 47 መሠረት በመንግስት የሚሰጥ ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ ወይም ዋስትና ነው።
3. "የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ተወካይ" ማለት በፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን ውስጥ እንዲያገለግል በመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል የሚመደብ የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ተወካይ ነው።
4. "የመግአ ፕሮጀክቶች ዝርዝር" ማለት በመግአ አሰራር እንዲተገበሩ የታመነባቸው በቅደም ተከተል የተቀመጡ ፕሮጀክቶች ዝርዝር ነው።
5. "የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን" ማለት በመግአ አዋጅ አንቀጽ 14 እና በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በተዋዋይ ባለስልጣን የሚቋቋም ቡድን ነው።
6. "የፕሮጀክት አፈጻጸም መከታተያ ሰነድ" ማለት የፕሮጀክት አፈጻጸምን በመከታተል ተዋዋይ ባለስልጣንና የግሉ ባለሀብት በፕሮጀክት ስምምነቱ መሠረት ኃላፊነታቸውን እየተወጡ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲረዳ በመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል የሚዘጋጅ ዝርዝር የፕሮጀክት አፈፃፀም መለኪያዎችን የያዘ ሰነድ ነው።





የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2

## 4. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የመንግስትና የግል አጋርነት አዋጅ ተፈጻሚ በሚሆንባቸው የመንግስትና የግል አጋርነት ፕሮጀክቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የመንግስትና የግል አጋርነት አስተዳደር

## 5. የመንግስትና የግል አጋርነት ቦርድ

1. ቦርዱ ዘጠኝ አባላት የሚኖሩት ሲሆን ሰባቱ ከመንግስትና ሁለቱ ደግሞ ከግሉ ዘርፍ የሚወከሉ ይሆናል፡፡

2. የቦርዱ ሰብሳቢ በቦርዱ ውስጥ የግሉን ዘርፍ የሚወክሉ ተወካዮች እንዲመረጡ በማድረግ የግሉ ዘርፍ ውክልና በቦርዱ ውስጥ መሟላቱን ያረጋግጣል፡-

   ሀ/ የቦርድ ሰብሳቢ በቦርዱ ውስጥ የግሉን ዘርፍ እንዲወክሉ የሚመረጡ ግለሰቦች ያላቸውን ሙያ፣ በግል የንግድ ድርጅቶች ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ወይም የኃላፊነት ደረጃ፣ በኩባንያዎች ውስጥ ያላቸውን አክስዮን ወይም ሌሎች ጥቅሞች እና የሚሰጡት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ካለ እንዲያሳውቁ ይጠይቃል፡፡

   ለ/ በየጊዜው ሊታደስ የሚችል ሆኖ የግሉን ዘርፍ የሚወክሉ ግለሰቦች የአገልግሎት ዘመን ሦስት ዓመት ይሆናል፡፡

3. ከግል ዘርፍ የተወከሉ የቦርድ አባላት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 29 ላይ የተጠቀሱትን የስነ-ምግባር ግዴታዎች መጣሳቸው ከተረጋገጠ ያለማስጠንቀቂያ በማንኛውም ጊዜ ከአባልነት ሊነሱ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ከመንግስት የተወከሉት የቦርድ አባላት ተመሳሳይ የስነ-ምግባር ጥሰት ሲፈጽሙ በመንግስት አሰራር ስርዓት መሰረት ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

4. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ዋና ዳይሬክተር የቦርዱ ጸሐፊ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በማንኛውም የቦርዱ ስብሰባዎች ላይ ድምጽ የማይሰጥ ሆኖ ይሳተፋል፡፡

## 6. የመንግስትና የግል አጋርነት ቦርድ ስብሰባ

1. የቦርዱ ውሳኔዎች በጽሑፍ የሚደረጉ ሆነው ሁሉም የቦርድ ውሳኔዎች በስብሰባው ወቅት መተላለፍ ይኖርባቸዋል፡፡

2. ቦርዱ መደበኛ ስብሰባዎቹን በየሶስት ወሩ ያደርጋል፡፡ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ የቦርዱ ሰብሳቢ በማንኛውም ጊዜ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

3. የቦርድ ስብሰባ ማሳወቂያ ደብዳቤ የስብሰባውን አጀንዳ፣ ቦታና ሰዓት መግለጽ አለበት፡፡ ቦርዱ በተለየ ሁኔታ ካልተስማማ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት ካልተወሰነ በስተቀር የቦርዱ ስብሰባ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ውስጥ ይካሄዳል፡፡

4. በቦርዱ ስብሰባዎች ላይ ሰብሳቢውን ጨምሮ ቢያንስ ስድስት የቦርዱ አባላት ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ እንደተሟላ ይቆጥራል፡፡

5. የመንግስትን ተቋማት የሚወክሉ የቦርዱ አባላት ሚኒስትር ወይም የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ ይሆናሉ፡፡

6. እንደየሁኔታው የቦርዱ አባላት የቦርዱ ስብሰባ ላይ በአካል ወይም ተስማሚ የኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ተጠቅመው ባሉበት ሆነው መሣተፍ ይችላሉ፡፡ ማንኛውም የቦርድ አባል በስብሰባ መገኘት የማይችልበት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ሲያጋጥመው ጉዳዩን ከስብሰባው ሶስት ቀን አስቀድሞ ለቦርድ ሰብሳቢ ማሳወቅ አለበት፡፡

7. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (6) ቢኖርም የቦርዱ አባላት በአዋጁ አንቀፅ 18 መሰረት ፕሮጀክቶችን በማጽደቅ ወደ ጨረታ እንዲገቡ ውሳኔ በሚሰጥባቸው ስብሰባዎች ላይ በአካል መገኘት ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም በአንድ ጊዜ ስብሰባ ወደ ጨረታ የሚገቡ ፕሮጀክቶችን ማፅደቅ ካልተቻለ ማንኛውንም ተስማሚ የኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘዴን በመጠቀም በሚደረግ ስብሰባ ውሳኔ ሊተላለፍ ይችላል፡፡

8. እያንዳንዱ የቦርድ አባል አንድ ድምፅ ብቻ ይኖረዋል፡፡

9. ማንኛውም የቦርዱ ውሳኔ የሚተላለፈው በስብሰባው ከተገኙት አባላት በአብላጫ ድምፅ ሲደገፍ ነው፡፡ ሆኖም የአባላቱ ድምጽ እኩል በኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡

10. ማንኛውም የቦርድ አባል ድምፅ በሚሰጥበት ማናቸውም ጉዳይ ላይ ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ ጥቅም ያለው ከሆነ ይህንኑ ለቦርዱ ሰብሳቢ በማሳወቅ በጉዳዩ ላይ ድምፅ ከመስጠት ራሱን ማግለል አለበት፡፡

11. ማንኛውም በቦርዱ ስብሰባ ላይ የሚሣተፍ ግለሰብ በቦርድ ስብሰባ አጋጣሚ ያወቀውን ወይም ያገኘውን መረጃ በሚስጥር የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

## 7. <u>የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል</u>

1. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል በአዋጁ አንቀጽ 12(2) መሰረት ለተዋዋዩ ባለስልጣን የሚሰጠው የቴክኒክ ድጋፍ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

   ሀ/ ቦርዱ በመግአ እንዲያዙ ለወሰናቸው ፕሮጀክቶች ከተዋዋይ ባለስልጣን ጋር በመተባበር አስፈላጊ የትራንዛክሽን አማካሪዎች እንዲኖሩት እገዛ ያደርጋል፤



የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት

ለ/ በፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን ውስጥ ከፕሮጀክት ዝግጅት እስከ አፈጻጸም ሂደት ውስጥ በንቃት የሚሣተፍ የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ተወካይ የሚሆን ባለሙያ ይመድባል፤

ሐ/ በተዋዋይ ባለስልጣን የፕሮጀክት በድን ውስጥ የተመደበው የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ተወካይ የተጣለበትን ኃላፊነት በተገቢው ሁኔታ እንዲወጣ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል ይከታተላል፤

መ/ የፕሮጀክት ስምምነትና የጨረታ ሰነዶች ዝግጅት ላይ ተዋዋይ ባለስልጣኑ በትራንዛክሽን አማካሪዎች በመደገፍ እንዲያዘጋጁ ያደርጋል፤ የሰነዶቹን ጥራት ያረጋግጣል፡፡

ሠ/ ለፕሮጀክቱ የተመደቡ ትራንዛክሽን አማካሪዎች ለተዋዋይ ባለስልጣንና ለመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ወቅታዊና መደበኛ ሪፖርት እያደረጉ መሆኑን ይከታተላል፤

ረ/ የመግአ ፕሮጀክት ለአሸናፊው የግል ባለሀብት ከተላለፈ በኋላ የመግአ ፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን የፕሮጀክት ስምምነት ሰነዶችን በትክክል መረዳታቸውን እንዲሁም የፕሮጀክት ስምምነቱን ለመፈጸም አስፈላጊ ድጋፍና እገዛዎች መስጠቱን ያረጋግጣል፡፡

2. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል የግል ባለሀብትን በሚመርጥበት ወቅት፡-

ሀ/ በተዘጋጀው የፕሮጀክት ስምምነት ሰነድና እና የጨረታ ሰነድ በመጠቀም ማንኛውም የመረጣ ሂደት ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፤

ለ/ አግባብነት ያላቸው የተዋዋይ ባለስልጣን ፍላጎትና ጥያቄዎች በሁሉም የግል ባለሀብት መረጣ ሂደቶች ውስጥ ግምት ውስጥ መግባታቸውን ያረጋግጣል፤

ሐ/ ተዋዋይ ባለስልጣኑ የግል ባለሀብቱን በመምረጥ ሂደት ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ እንዲኖረው ያመቻቻል፤ መሳተፉንም ያረጋግጣል፤

መ/ ከተወዳዳሪ የግል ባለሀብቶች ጋር በሚደረግ ውይይት መነሻነት በጨረታ ሰነዶች ላይ በሚኖር ማሻሻያ ላይ የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን ተሳትፎ እንዲያደርግ ያመቻቻል፤

## 8. ማኑዋሎች

1. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል የመንግስትና የግል አጋርነት አተገባበርን ለማሳለጥ የሚያዘጋጃቸው ማንዋሎች ቢያንስ የሚከተሉትን መሰረታዊ ጉዳዮች ማካተት አለባቸው፡፡

ሀ/ በመግአ ሊታቀፉ የሚችሉ ፕሮጀክቶች የሚለዩበትና የሚመረጡበትን መመዘኛ (Project Screening Criteria) ፤



የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት

ለ/ የአዋጭነት ጥናቶች የሚገመገሙባቸውን መስኪያዎች (Project Feasibility and Appraisal Criteria)፣

ሐ/ ለገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ መገኘቱ የሚወሰንበትን መመዘኛ (Value for Money)፣

መ/ የመንግስትን ድጋፍ ለመጠየቅ የሚያስችሉ መስፈርቶች፣

ሠ/ ሞዴል የፕሮጀክት ስምምነቶች ፣

ረ/ የመግአ ኮንትራት አስተዳደር አሠራሮች፣

2. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል የመግአ የፕሮጀክቶች ዝግጅትና አፈጻጸም ግምገማን መሠረት በማድረግ የሚያዘጋጃቸውን ማኑዋሎች በየጊዜው ማሻሻል አለበት፡፡

3. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል የሚያዘጋጃቸውን ማኑዋሎች ለባለድርሻ አካላት በቀላሉ ተደራሽ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት
## የተዋዋይ ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት

## 9. ተዋዋይ ባለስልጣን

1. በመግአ አዋጅ አንቀጽ 16 መሠረት ቦርዱ አንድን ፕሮጀክት በመግአ አሠራር እንዲተገበር ከፈቀደ በኋላ ተዋዋይ ባለስልጣን የመግአ ፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን ያቋቁማል፡፡ የመግአ ፕሮጀክት አስተዳደር ቡድንን በማቋቋም ረገድ የተዋዋይ ባለስልጣኑ፡-

   ሀ/ የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኑን ለማቋቋም አስፈላጊ ድጋፍ እንዲሰጠውና እንዲሁም ተወካይ እንዲመደብለት የመግአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራልን ይጠይቃል፤

   ለ/ ከራሱ ባለሙያዎች የፋይናንስ፣ የቴክኒክ፣ የሕግ እንዲሁም ፕሮጀክቱን ለማዘጋጀት፣ ለማስተዳደርና ለመተግባር ዕውቀትና ክህሎት ያላቸውን ባለሙያዎች ይመርጣል፣ ይመድባል፤

   ሐ/ ለፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን ከተመደቡት ባለሙያዎች መካከል በዋናነት የፕሮጀክት ዝግጅት ሥራዎች ላይ ውሳኔዎችን የሚሰጥ የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን መሪ ይሰይማል፤

   መ/ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለመግአ ፕሮጀክት ስራ በመግአ ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ሲፈቀድ የመግአ ትራንዛክሽን አማካሪዎችን ለመቆጣጠር የሚያስፈልገውን የፋይናንሻል፣ ቴክኒካልና የሕግ ክህሎት ያለውን ባለሙያ በመቅጠር ሊያሰራ ይችላል ወይም ተጨማሪ አማካሪ ሊቀጥር ወይም ሊመድብ ይችላል፡፡





የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት

2. ተዋዋይ ባለስልጣኑ የፕሮጀክቱን አፈጻጸም ለማሳለጥ የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን በሚያቋቋምበት ወቅት እንደአስፈላጊነቱ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የሌሎች ቁልፍ ባለድርሻ ተቋማት ተወካይ ሊያካትት ይችላል፡፡ ባለሙያዎቹ ቋሚ የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን አባል ሳይሆኑ ቴክኒካል ዕውቀታቸው ሲፈለግ በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ ይችላል፡፡

3. ተዋዋይ ባለስልጣኑ በመግአ አዋጅ መሰረት የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኑ የተሰጠውን ኃላፊነት መወጣቱን በየጊዜው በመከታተል ማረጋገጥ አለበት፡፡

4. ተዋዋይ ባለስልጣኑ በመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል በኩል የተላከለትን የፕሮጀክት ስምምነት ከመፈረሙ በፊት አስፈላጊ የሆኑ የማስፈቀድ ሥራዎችን የማከናወን ኃላፊነት አለበት፡፡

## 10. <u>የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን</u>

1. የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኑ በመግአ ፕሮጀክት ዝግጅት ወቅት በየጊዜው ስብሰባ በማድረግ በፕሮጀክት አዋጭነት እና ሌሎች ጥናቶች እንዲሁም በፕሮጀክት ቅርፅ ዝግጅት፣ በፕሮጀክት ስምምነቶች ዝግጅት እና ጨረታ ሰነድ ዝግጅት እንዲሁም በስራ ላይ ባለው የመግአ ፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ውይይት ማድረግ አለበት፡፡

2. የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኑ በሚያወጣው የስበስባ መርሀ ግብር መሰረት መሰብሰብ የሚችል ሆኖ ፡-

   ሀ/ ሁሉም የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን አባላት መገኘት እንዲችሉ የቡድን መሪው ቀደም ብሎ ስለሚኖሩ ስብሰባዎች በአግባቡ ማሳወቅ አለበት፤

   ለ/ ሁሉም የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን አባላት በሁሉም ውይይቶች ላይ በተከታታይ መሳተፍ ያለባቸው ሲሆን፤ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥም ለቡድን መሪው ማስታወቅ አለባቸው፤

   ሐ/ የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን አባላት የጥቅም ግጭት በፕሮጀክት ዝግጅትና ትግበራ ወቅት የሚኖር ከሆነ ወይም እንደሚኖር ከተገመተ ወይም እንዳለ ካወቁ ወዲያው ለቡድን መሪው በማሳወቅ በጉዳዩ ላይ ስለሚኖራቸው ተሳትፎ የቡድኑን ምክር ወይም ውሳኔ ማግኘት ይኖርባቸዋል፡፡

3. የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኑ እንደሁኔታው በመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል እና በትራንዛክሽን አማካሪዎች በመታገዝ የጨረታ ሰነድ እና የፕሮጀክት ስምምነት ማዘጋጀት አለበት፡፡

4. የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኑ በትራንዛክሽን አማካሪዎች የተዘጋጁ ከፕሮጀክት ዝግጅት ጋር የተገናኙ ሰነዶችን ወይም የምክር ሀሳቦችን በመገምገም ለተዋዋይ ባለስልጣኑ ወይም ለመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ያቀርባል፡፡

5. የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን አባላት የተሰጣቸውን የፕሮጀክት መረጃዎች በሚስጥር የመጠበቅ ኃላፊነት አለባቸው፡፡



የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር
የሪከርድ
አስተዳደር

6. በመግአ አዋጅ ውስጥ ከተዘረዘሩት ኃላፊነቶች በተጨማሪ የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኑ ፕሮጀክቱ በተያዘለት ዕቅድ መሰረት እየሰራ መሆኑንና ተዋዋይ ባለስልጣኑም ሆነ የግል ባለሀብቱ በፕሮጀክት ስምምነቱ መሠረት ኃላፊነታቸውን መወጣታቸውን ለማረጋገጥ የሚረዳ የፕሮጀክት አፈጻጸም መከታተያ ሰነድ ያዘጋጃል፤ የሰነዱ ይዘትና ጥራት በመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል እንዲረጋገጥ ይደረጋል፤ በሰነዱ መሰረት የተዘጋጀውን ሪፖርት ለተዋዋይ ባለስልጣንና ለመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ያቀርባል፡፡

7. የፕሮጀክት ስምምነት ከተፈረመ በኋላ ተዋዋይ ባለስልጣን እንደገና በፕሮጀክት ስምምነቱ ላይ መደራደር የሚያስፈልግበት ሁኔታ ቢያገጥም የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን የድርድሩን አስፈላጊነትና ውጤት የሚያስከትለውን ለውጥ ለመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ማሳወቅ አለበት፡፡ በመግአ አዋጅ አንቀጽ 9 ንዑስ ቁጥር 1(ሐ) መሠረት የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ይህንኑ ለቦርዱ አቅርቦ ማስጸደቅ አለበት፡፡

## ምዕራፍ አራት

## <u>የመንግስትና የግል አጋርነት ዝግጅትና የማጽደቅ ሂደት</u>

### 11. <u>ፕሮጀክቶችን የመለየት ስራ</u>

1. በመሠረተ-ልማት ዕቅድ ወይም በህዝብ አገልግሎት ማስፋፋት ሂደት ውስጥ ከግል ባለሀብት ጋር በመግአ እንዲተገበሩ የሚያስፈልጉ ፕሮጀክቶችን፤ ተዋዋይ ባለስልጣን ወይም መንግስታዊ ተቋም ወይም የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል በመለየት ማቅረብ ይችላሉ፡፡

2. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል በመግአ ስልት ሊተገበሩ የሚችሉትን ፕሮጀክቶች ዝርዝር በቅደም ተከተል ይይዛል፣ ከተዋዋይ ባለስልጣን ወይም ከሌሎች መንግስት ተቋማት የተገኘውን መረጃ በመጠቀም የፕሮጀክቶች ወቅታዊ መረጃ ይይዛል፡፡

3. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል በመግአ እንዲያዙ የሚያስፈልጉ ፕሮጀክቶችን በተቀመጠው መመዘኛ መሰረት በመለየት ለቦርዱ ይሁንታ በሚቀርበው የመግአ ፕሮጀክቶች ዝርዝር ውስጥ እንዲካተቱ በመወሰን ያቀርባል፡፡ የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ይህንን ሲያደርግ ለዚህ ተግባር የወጣውን የአሰራር ስርዓት ይከተላል፡፡

### 12. <u>በቦርድ ስለሚሰጥ የቅድሚያ ፈቃድ</u>

1. በመግአ አዋጅ አንቀጽ 16 መሠረት ቦርዱ ማንኛውንም ፕሮጀክት በመግአ መልክ እንዲተገበር ሲፈቅድ የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት ውስጥ ያስገባል፡-

   ሀ/ ፕሮጀክቱ ከኢትዮጵያ ልማት ፖሊሲ ዓላማዎች ጋር የተጣጣመ መሆኑን፣



የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር
የሪከርድ አስተዳደር

ለ/ ፕሮጀክቱ ለሚያስገኘው ምርት ወይም አገልግሎት በቂ ፍላጎት መኖሩን፣

ሐ/ ፕሮጀክቱ ትርጉም ያለው ህዝባዊ ጠቀሜታ የሚያስገኝ መሆኑን፤ በመንግስት ከሚያዝ ይልቅ በግሉ ዘርፍ ቢያዝ የተሻለ መሆኑንና እንዲሁም ተገቢውን የፕሮጀክት ስጋቶች ለግል ባለሀብቱ ለማስተላለፍ ዕድል የሚሰጥ መሆኑን፣

መ/ ፕሮጀክቱ ለገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ ማስገኘቱን (Value for Money)፣

ሠ/ የሚጠበቀውን የመንግስት ድጋፍ ጨምሮ ለፕሮጀክቱ በቂ የፋይናንስ ሀብት ማቅረብ የሚቻል መሆኑን፣እና

ረ/ ተዋዋይ ባለስልጣን ፕሮጀክቱን ለማዘጋጀት እና ተግባራዊ ለማድረግ በቂ ሀብትና አቅም ያለው መሆኑን፤

2. ቦርዱ ፕሮጀክቶች በመግአ እንዲተገበሩ ሲፈቅድ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሳይወሰን በፕሮጀክት ዝግጅት ሂደት መሟላት ስለሚኖርባቸው ሁኔታዎች ሊወስን ይችላል፤

ሀ/ የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድኑ የመግአ ፕሮጀክትን በሚያዘጋጅበት ወቅት ሊከተላቸው የሚገቡ ሁኔታዎችን፣

ለ/ በተዋዋይ ባለሥልጣን ስር ለሚቋቋም የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን ስለሚያስፈልገው የሰው ሀብትና የሙያ ስብጥር ፣

## 13. <u>የአዋጭነት ጥናት</u>

1. ተዋዋይ ባለስልጣኑ የአዋጭነት ጥናቱን የሚያዘጋጀው የመንግስትና የግል አጋርነት ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ባወጣው የመግአ ማኑዋል መሠረት ነው።

2. በመግአ አዋጅ አንቀፅ 17 (2) ከተዘረዘሩት ጉዳዮች በተጨማሪ የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን የሀገር ውስጥ የግል ባለሀብት በማንኛውም የመግአ ፕሮጀክት ላይ የሚሳተፍበትን አማራጭ ስለመኖሩ ይገመግማል።

3. በአዋጭነት ጥናት ውጤት መሰረት፣ የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ከሚኒስቴሩና ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ጋር በመተባበር የመግአ ፕሮጀክቶችን ለመተግበር ታሳቢ የሆኑ ግዴታዎች ትንታኔ ከሌሎች ፕሮጀክቶች ጋር በማነጻጸርና ከፋይናንስ ግዴታዎች ጋር በተያያዘ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችን በሚያሳይ መልኩ ያዘጋጃል።

4. ከተዋዋይ ባለስልጣን የሚቀርብ የመግአ አዋጭነት ጥናት፤ በመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ተገምግሞ ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለቦርድ ውሳኔ መቅረብ አለበት።



የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር
የሪከርድ
አስተዳደር
አገልግሎት

## 14. ወደ ጨረታ ለመግባት በቦርዱ ስለማጽደቅ

1. በአዋጁ አንቀጽ 18 መሰረት ተዋዋይ ባለስልጣን ለሚያከናውነው ፕሮጀክት የግል ባለሀብት ለመምረጥ ጨረታ እንዲወጣ በቦርዱ ለማፀደቅ በመግአ ማንዋል መሰረት አዘጋጅቶ ከሚያቀርበው ደረጃውን የጠበቀ የአዋጭነት ጥናት በተጨማሪ የሚከተሉትን ሰነዶች አሟልቶ ማቅረብ አለበት፡-

   ሀ/ ፕሮጀክቱን የሚፈፅመው የግል ባለሀብት የሚመረጥበትን የጨረታ ዕቅድ ጨረታው የሚፈፀምበትን ሂደት ከሚያሳይ ሰነድ ጋር፣ የፕሮጀክቱ ስምምነት የሚመሰረትባቸውን ዋና ዋና የውል ቃሎችና ሁኔታዎች (Heads of terms for Project) ወይም የፕሮጀክት ስምምነቱን ረቂቅ ሰነድ፣

   ለ/ የፕሮጀክት ስምምነቱ ከመፈረሙ በፊት ለፕሮጀክቱ አፈፃፀም የሚያስፈልጉ አግባብ ካላቸው የመንግስት አካላት የተሰጡ የፈቃድ ሰነዶች፣

   ሐ/ የአዋጭነት ጥናቱ ከመጽደቁ በፊት እንደ ፕሮጀክቱ ባህሪ ሊረጋገጡ የሚገባቸው ልዩ ሁኔታዎች ካሉ በተዋዋይ ባለስልጣን በኩል ታይተው ስለመረጋገጣቸው የሚገልጽ ሰነድ፤

2. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ተዋዋዩ ባለስልጣን በቦርዱ እንዲጸድቅለት ያቀረበውን የአዋጭነት ጥናት በመገምገም ለቦርዱ በሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ የሚከተሉት ነጥቦች መካተታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡-

   ሀ/ በተዋዋዩ ባለሥልጣን የቀረበው የአዋጭነት ጥናት አግባብነት ባላቸው ሰነዶች የተደገፈና በዚሁ መሰረት ፕሮጀክቱ በመግአ ማዕቀፍ ቢሰራ የሚያዋጣ መሆኑን፤

   ለ/ እንደፕሮጀክቱ ባህሪ የግል ባለሀብቱን ለመምረጥ ተገቢ የሆነውን የግል ባለሀብት መምረጫ ዘዴ ወይም የጨረታ ዕቅድ በተጨባጭ አስረጂ ነጥቦች ተደግፎ የቀረበ መሆኑን ፣

   ሐ/ የግል ባለሀብቱ የሚመረጥባቸው ዋና ዋና የግምገማ መስፈርቶች እንዲሁም እንደአግባብነቱ የፕሮጀክት ስምምነቱ የሚመሰረትባቸውን መሰረታዊ የውል ቃሎችና ሁኔታዎች ማካተቱን።

3. ፕሮጀክቱ በሚጸድቅበት ወቅት ተዋዋዩ ባለስልጣን በቦርዱ ስብሰባ ላይ ተገኝቶ ፕሮጀክቱን ለቦርዱ ማስረዳት እንዲሁም ከቦርዱ ለሚቀርቡለት ጥያቄዎች ላይ መልስ የመስጠት መብት ይኖረዋል።

4. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል የጨረታ ሂደቱን እንዲያካሄድ ሲፈቀድለት፣ በመግአ አዋጅ አንቀጽ 18 (4) መሠረት ቦርዱ ከሚመለከተው የመንግስት ተቋም የመንግስት ድጋፍ ወይም ዋስትና መገኘቱን በማረጋገጥ ጨረታውን እንዲያወጣ ካልፈቀደ በስተቀር የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ጨረታ ማውጣት አይችልም።





የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት

5. በጨረታ ወቅት ወይም የፕሮጀክት ስምምነቱ ከተፈረመ በኋላ በድርድር የፕሮጀክቱ ቅርፅ ትርጉም ባለው መልኩ የሚቀየር ከሆነ የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል የተዋዋይ ባለስልጣኑን የፕሮጀክት አስተዳደር ቡድን በማሳተፍ የለውጡን ተፅዕኖ በሚያሳይ መልኩ በጥልቀት ተንትኖ ለቦርዱ ውሳኔ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

## 15. የመንግስት ድጋፍ

ለፕሮጀክት ስምምነት በመግአ አዋጅ አንቀጽ 47 መሠረት የመንግስት ድጋፍ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንዲሁም በሕግ የተጣለ የመንግስት ድጋፍ በሚመለከተው የመንግስት ባለስልጣን የማስጸደቅ ግዴታ እስከሌለ ድረስ ቦርዱ በመግአ አዋጅ አንቀጽ 18 እና 32 መሰረት የመግአ ፕሮጀክትን ማጽደቁ በራሱ ተፈላጊውን የመንግስት ድጋፍ እንደማስጸደቅ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ አምስት
## የግል ባለሀብትን ስለመምረጥ

## 16. ብቃት ማረጋገጥ

1. ፕሮጀክቱን ለማስፈጸም ከግል ባለሀብቱ የሚፈለገውን ብቃት ለማስታወቅና የተቻለውን ያህል ተጫራች ለመጋበዝ ሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ የጥሪ ማስታወቂያ ቢያንስ አንድ ጊዜ መውጣት ይኖርበታል፡፡ የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ይህንኑ ጥሪ በራሱ፣ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲሁም በተዋዋይ ባለስልጣኑ ድህረ-ገጽ ላይ ማውጣት አለበት ፡፡

2. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ከጋዜጣ ጥሪ በተጨማሪ ለመጫረት እንደሚችሉ ለይቶ ለሚያውቃቸው ተጫራቾች ጥሪውን በቀጥታ መላክ ይችላል፡፡

3. የብቃት ማረጋገጫ ጥያቄ ይዘት ቢያንስ የሚከተሉትን ጉዳዮች ሊያካትት ይገባል፡-

   ሀ/ ከፕሮጀክቱ ጋር የተገናኙ አጠቃላይ መረጃዎችን፣

   ለ/ ለፕሮጀክቱ መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮች፣ ለምሳሌ ከፕሮጀክቱ የሚጠበቀው አገልግሎት እና ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልገው ፋይናንስ የሚቀርብበት ሁኔታ፣

   ሐ/ የሚታወቅ ከሆነ የፕሮጀክት ስምምነቱ የሚመሰረትባቸው ዋና ዋና የውል ቃሎች፣

   መ/ የቅድመ-ብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች እና፣

   ሠ/ የብቃት ማረጋገጫ የሚቀርብበት አኳኋንና የማቅረቢያ ቀነ ገደብን፡፡



የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት

## 17. የቅድመ-ብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች

1. በብቃት ማረጋገጫ መጠየቂያ ውስጥ የሚካተቱ የቅድመ-ብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች ቢያንስ የሚከተሉትን ነጥቦች ሊይዙ ይገባል፡፡

   ሀ/ በማንኛውም የፕሮጀክቱ አፈፃፀም ደረጃ ሥራውን በአግባቡ ማከናወን የሚያስችል በቂ የሙያ እና የቴክኒክ ብቃት ያላቸው ባለሙያዎች መኖራቸውን፣

   ለ/ የፕሮጀክቱን የፋይናንስ አስተዳደር መምራት የሚያስችል ብቃት እና የፕሮጀክቱን የፋይናንስ ፍላጐት በዘላቂነት ማሟላት የሚያስችል አቅም፣

   ሐ/ አስፈላጊ አስተዳደራዊ እና ድርጅታዊ አቅም፣ አስተማማኝነት እና ልምድ፣ ቀደም ሲል ተመሳሳይ የመሰረተ ልማት ግንባታና የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ ስራዎች ላይ ያለን ልምድ ፡፡

2. የብቃት መመዘኛዎች በሚከተሉት መሰረት በማስረጃ መረጋገጥ አለባቸው፡-

   ሀ/ የቴክኒክ፣ የፋይናንስና የሥራ አመራር ብቃት በሚጠይቁ ተመሣሣይ ፕሮጀክቶች አፈፃፀም ጋር የተያያዘ ቀዳሚ የሥራ ልምድ ማስረጃ፣

   ለ/ የፋይናንስ አቅምን በተመለከተ የኩባኒያው የተጣራ ዋጋ (net worth)፣ የተጣራ ገቢ (net turnover) ወይም ሌሎች አስፈላጊ የፋይናንስ መስፈርቶች፣ በኦዲት የተረጋገጡ የሂሳብ መግለጫዎች ወይም ሌሎች አግባብነት ያላቸው የፋይናንስ ሰነዶች ፤

   ሐ/ የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል አስፈላጊ ናቸው ያላቸው ሌሎች መስፈርቶች፤

3. ለዓይነተኛ የመግአ ፕሮጀክቶች በተለይ የሚያስፈልጉ የቅድመ-ብቃት ማረጋገጫ መስፈርቶች የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል በሚያወጣው ማኑዋል ውስጥ በዝርዝር ይቀመጣሉ፡፡

## 18. የመወዳደሪያ ሀሳብ ስለመጠየቅ

1. በመግአ አዋጅ ውስጥ ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የመወዳደሪያ ሀሳብ፡-

   ሀ/ መከተል የሚገባውን የግል ባለሀብት አመራረጥ ሂደት በግልፅ ማስቀመጥ አለበት፤

   ለ/ እንዳስፈላጊነቱ ተጫራቾች በጨረታ ማቅረቢያ ነጥቦችና በፕሮጀክት ስምምነቶች ላይ አስተያየት የሚሰጡበትን ሂደት በግልጽ ማሳየት አለበት፤

   ሐ/ ተጫራቾች ማብራሪያ የሚጠይቁበትን ጊዜ እና ሂደት መግለጽ አለበት፤

   መ/ ተጫራቾች ሊያሟሉ የሚገባቸውን መሰረታዊ መመዘኛዎችና ሁኔታዎችን ማሳየት አለበት፤



የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር
የሪከርድ
አስተዳደር
አገልግሎት

ሠ/ የቴክኒክና ፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ አቀራረብ ወጥነት እንዲኖረው ማድረግ አለበት፤

ረ/ የመወዳደሪያ ሀሳቡ የሚቀርብበትን ጊዜና ቦታ በግልጽ ማመልከት አለበት፤

ሰ/ ግልጽ ያልሆኑ ጉዳዮች ካሉ ተጫራቹ መረጃ ወይም ማብራሪያ የሚያገኝበትን አድራሻ ማስቀመጥ አለበት፤

ሸ) የቴክኒክና የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቦች የሚቀረቡበትን መንገድና የግምገማ ስርዓቱን ግልጽ ማድረግ አለበት።

## 19. የጨረታ ዋስትና

1. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ተጫራቾች የጨረታ ዋስትና እንዲያቀርቡ መጠየቅ አለበት።

2. የመግአ ዳሬክቶሬት ጄኔራል ለጨረታ ዋስትና የተጠየቀው ዓይነት፣ ቅርፅ፣ መጠን እና ሌሎች ዋና ዋና ጉዳዮች በገበያ ልምድ ውስጥ የሚታወቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት።

3. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትናው መጠን ተጫራቾች የተሳተፉበትን ጨረታ እንዲያከብሩ የሚያነሳሳ ሆኖ፣ የመጫረቻ ዋጋ በማናር ተሳታፊዎችን እንዳይሳተፉ የሚያደርግ ወይም አላግባብ ለጨረታ ዝግጅት ተጫራቾች የሚያወጡትን ወጪ በማነር እንዳይሳተፉ የሚያደርግ መሆን የለበትም።

4. አንድ ተጫራች ከዚህ በታች በተመለከቱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር ያስያዘው የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ሊወሰድበት አይችልም፡-

   ሀ/ የመወዳደሪያው ሀሳቡ ማስረከቢያ ቀነ-ገደብ ከተጠናቀቀ በኋላ የመጫረቻ ሰነዱን መልሶ በመውሰድ ከውድድሩ መውጣት ወይም ባቀረበው የመወዳደሪያ ሀሳብ ላይ ማሻሻያ ማድረግ፤

   ለ/ በመግአ አዋጅ አንቀጽ 31 መሠረት የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል አስፈላጊነቱን በማመን በሚያደርገው ጥሪ መሰረት ቀርቦ ድርድር ለማድረግ አለመቻል፣

   ሐ/ ተጫራቹ አሸናፊነቱ ከተገለጸለት በኋላ የመንግስት የግል አጋርነት ስምምነትን እንዲፈርም ሲጠየቅ በተወሰነው ጊዜ ቀርቦ ሳይፈርም ቢቀር ወይም ፤

   መ/ አሸናፊነቱ ከተገለጸለት በኋላ የፕሮጀክት ስምምነት ግዴታውን ለመወጣት የሚጠየቀውን የሥራ አፈፃፀም ዋስትና ያላቀረበ እንደሆነ ወይም የፕሮጀክት ስምምነቱ ከመፈረሙ በፊት በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ የተገለፀውን ሌላ ማንኛውንም ቅድመ ሁኔታ ያላሟላ እንደሆነ፣



የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት

## 20. የመወዳደሪያ ሀሳቦችን ስለመገምገም

1. የቴክኒካዊ መወዳደሪያ ሀሳብ ግምገማ እና የማወዳደሪያ መስፈርቶች ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፤

   ሀ/ ቴክኒካዊ ብቃት፤

   ለ/ ከአካባቢ ጥበቃ መመዘኛዎች ጋር መጣጣም፤

   ሐ/ ሊተገበር የሚችል መሆኑ፤

   መ/ የአገልግሎቱን ወይም ምርቱን ጥራት እና ቀጣይነት ለማረጋገጥ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ያካተተ መሆኑ፤

2. የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳቦችን ለመገምገምና ለማወዳደር የሚረዱ መስፈርቶች በፕሮጀክቱ ዓይነት ላይ የተመሰረቱ ይሆናል። የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ለዚህ አፈፃፀም ዝርዝር ማኑዋል ያወጣል።

3. የሀገር ውስጥ ተሳትፎን ለማበረታታት ሲባል የሀገር ውስጥ ባለሀብት የካፒታል ድርሻ ከ 50% የሚበልጥ ሆኖ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ሲሟሉ በመግአ ፕሮጀክት መሳተፍ ለሚፈልግ ኩባንያ ተወዳዳሪዎች በሚያቀርቡት የፋይናንስ መወዳደሪያ ሀሳብ ግምገማ ነጥብ ውስጥ እስከ 7% (ሰባት በመቶ) ልዩ አስተያየት እንደሚደረግ በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ጥሪ ሊገለጽ ይችላል።

   ሀ/ ግንባታን የሚያካትት ፕሮጀክት ሲሆን ቢያንስ 30% ጥሬ ዕቃ ከኢትዮጵያ የሚጠቀም ከሆነና ከጠቅላላ ሰራተኞቹ 50% ኢትዮጵያዊያን ሰራተኞችን ከሆኑ፤

   ለ/ በኩባንያው አመራር ከሚሳተፉት ሰዎች ከ50% የማያንሱት ኢትዮጵያዊን ሲሆኑ ።

   ሐ/ ግንባታን የማያካትት ፕሮጀክት ሲሆን እንደ ፕሮጀክቱ ዓይነት የልዩ አስተያት ተጠቃሚ ለመሆን የሚጠየቀው መስፈርት በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ጥሪ የሚወሰን ይሆናል።

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 2 እና 3 የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ ከአገር ውስጥ ባለሀብቶች ጋር ጥምረት የሚፈጥሩ የውጭ ሀገር ባለሀብቶች የልዩ አስተያየት ተጠቃሚ ይሆናሉ።

## 21. አሸናፊውን ስለማሳወቅና ስምምነት ስለመፈራረም

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 30 መሠረት የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ስለጨረታው ውጤት ለተጫራቾች ካሳወቀበት ቀን ጀምሮ እስከ ሰባት ቀን ድረስ ተዋዋይ ባለስልጣን የፕሮጀክት ስምምነት መፈረም የለበትም።



የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር
የሪከርድ
አስተዳደር
አገልግሎት

2. የመንግስትና የግል አጋርነት ስምምነት በሚፈረምበት ወቅት የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል የጨረታውን ውጤት በሀገር ደረጃ በሚሰራጭ ጋዜጣና አመቺ በሆነ የህዝብ መገናኛ ሚዲያ የኮንትራቱን ዓላማና፣ የተዋዋዮቹ ስም፣ የክፍያው ሁኔታና ዋና ዋና የስምምነቱ ገጽታዎችን ማስታወቅ ይኖርበታል። የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ይህን መረጃ በራሱና በሚኒስቴሩ ድህረ-ገጽ ላይ ያወጣል።

3. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል እና ተዋዋይ ባለስልጣን ተጫራቾችን በመምረጥ ውል የመስጠት ሂደትን በተመለከተ ተገቢውን መረጃ መያዝ አለባቸው።

## ምዕራፍ ስድስት

## <u>በውድድር ላይ የተመሠረተ ውይይት</u>

### 22. <u>በውድድር ላይ የተመሠረተ ውይይት ለመጠቀም ሊሟሉ የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች</u>

በመግአ አዋጅ አንቀጽ 37 (1) መሰረት በውይይት ላይ የተመሰረተ ውድድርን ለመጠቀም አንድ ፕሮጀክት ውስብስብ ነው የሚባለው ተዋዋይ ባለስልጣኑ እና የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ፡-

1. የየራሳቸውን ፍላጎት ወይም ዓላማ ለማሟላት ወይም ለማሳካት መጠቀም ስለሚኖርባቸው ቴክኒካዊ ዘዴዎችን በተጨባጭ አብራርተው ማቅረብ ካልቻሉ እና/ወይም

2. የፕሮጀክቱን ሕጋዊ እና/ወይም የፋይናንስ ስርዓት በተጨባጭ መወሰን ያልቻሉ ሲሆን ነው።

## ምዕራፍ ሰባት

## <u>ቀጥታ ድርድር</u>

### 23. <u>ለቀጥታ ድርድር ሊሟሉ የሚገቡ ቅድመ-ሁኔታዎች</u>

በመግአ አዋጅ በአንቀጽ 39 የተደነገጉትን ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በመግአ አዋጅ አንቀፅ 39 ንዑስ ቁጥር 1(ለ) እና (ሬ) መሠረት የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል በቦርድ ሲፈቀድ በመንግስትና የግል አጋርነት ስምምነት ላይ በቀጥታ ለመደራደር የሚከተሉትን ቅድመ-ሁኔታዎች ማሟላት አለባቸው ፡፡

1. ፕሮጀክቱ እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጊዜ ውስጥ የሚጠናቀቅ እና ያስከትላል ተብሎ የሚገመተው የመነሻ ኢንቨስትመንት ወጪ ከመቶ አርባ ሚሊዮን ብር የማይበልጥ ከሆነ፤

2. ፕሮጀክቱ ከኢንዱስትሪያል እና ከሌላ የኢንቨስትመንት ስራ ጋር ተያያዥ ከሆነ እና አገልግሎቱ በኢንዱስትሪ ወይም የኢንቨስትመንት ስራው በተሰማራው ባለሀብት መከናወን ያለበትና ሌሎች ተጫራቾች በፕሮጀክቱ የመሳተፍ ፍላጎት ይኖራቸዋል ወይም በፕሮጀክቱ የሚሳተፉበት የተሻለ አማራጭ ይዘው ይቀርባሉ ተብሎ የማይታመን ሲሆን ነው። የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል አቅም ያላቸው የግል ባለሀብቶች ፍላጎታቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ፣ የመወዳደሪያ ዋጋ ወይም ሌሎች ፍላጎቶችን እንዲገልጹ የጋበዛቸው ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃና የተሰጠውን ምላሽ በመተንተን ለመግአ ቦርድ ያቀርባል። የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል በተመሳሳይ የፕሮጀክት ስራ ላይ ልምድ ካላቸውና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተዋቂ ከሆኑ ቢያንስ ከሶስት ያላነሱ ድርጅቶች ጋር ቀደም ብሎ ግንኙነት ማድረግ አለበት።

## ምዕራፍ ስምንት

## <u>በራስ ተነሳሽነት የሚቀርብ የፕሮጀክት ሀሳብ</u>

### 24. <u>በራስ ተነሳሽነት የፕሮጀክት ሀሳብ ካቀረበ የግል ባለሃብት ጋር ስለሚደረግ የመጀመሪያ ስምምነት</u>

1. በራስ ተነሳሽነት የቀረበው የፕሮጀክት ሀሳብ በመግአ አዋጅ አንቀጽ 43 (1) መሰረት በመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ተቀባይነት ካገኘ ሀሳቡን ያቀረበው የግል ባለሀብትና ተዋዋዩ ባለስልጣን በመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ድጋፍ ፕሮጀክቱ ለቦርዱ ከመቅረቡ በፊት ከቀረበው ሀሳብ ጋር በተያያዘ ሀሳብ አቅራቢው ባለሀብትና የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ስለሚኖራቸው መብትና ግዴታ ስምምነት ይገባሉ። ይህ ስምምነት ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

    ሀ/ በሀሳብ አቅራቢው የተዘጋጀውን ጥናት ይዘት ምስጢር ስለመጠበቅ፣

    ለ/ ሀሳቡን ያቀረበው የግል ባለሀብት ጨረታውን ያላሸነፈ እንደሆነ የፕሮጀክት ጥናቱን መብቶች ለተወያዩ ባለስልጣን ወይም ለሌላ ወገን ስለሚተላለፍበት መንገድና ሁኔታ ፣

    ሐ/ ሀሳቡን ያቀረበው የግል ባለሀብት ጨረታውን ያላሸነፈ እንደሆነ በመግአ አዋጅ አንቀጽ 43(4) መሰረት ጥናቱን ለማካሄድ ላወጣው ወጪ ስለሚከፈል የገንዘብ ካሳ ወይም በጨረታው ግምገማ ለሀሳብ አቅራቢው ስለሚሰጥ ተጨማሪ ነጥብ ፣ እና

    መ/ ፕሮጀክቱን ለማዘጋጀት ስሚወሰዱ አስፈላጊ የሆኑ ቀጣይ እርምጃዎችን መለየትና ኃላፊነትን ስለመደልደል፣



የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር
የሪከርድ
አስተዳደር
አገልግሎት
2

2. የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ለማስፈጸም የሚያስችል የስምምነት ሞዴል ያዘጋጃል፡፡

## 25. ስለ ማበረታቻ ነጥብ እና የወጪ ማካካሻ ገንዘብ

1. ሀሳቡን ያቀረበው የግል ባለሀብት ማንነት፣ የተጨማሪ ነጥብ አሰጣጥ ዝርዝር ወይም ሀሳቡን ላቀረበው የግል ባለሀብት ሊሰጠው ስለሚችለው የካሳ መጠን በውድድር ጨረታ ስነ-ሥርዓት ሰነድ ውስጥ መገለጽ ያለበት ሲሆን፣ የቅድመ-ብቃት ማረጋገጫ የሚካሄድ ከሆነ ይኸው በዚህ ጊዜ ውስጥ ቢገለጽ ይመረጣል፡፡

2. ሀሳቡን ላቀረበው የግል ባለሀብት በጨረታው ውድድር ሂደት ሊሰጠዉ ስለሚገባው ትክክለኛ የቴክኒክ ወይም የፋይናንስ መወዳደሪያ ተጨማሪ ነጥብ መወሰን አስቸጋሪ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ሀሳቡን ላቀረበው ተወዳዳሪ የሚሰጠውን ተጨማሪ ነጥብ ወይም በአሸናፊነት ባይመረጥ የሚከፈለውን የወጪ ማካካሻ ገንዘብ መጠን የመወሰን ስልጣን አለው፡፡

3. ለሀሳብ አቅራቢው ባለሀብት የሚከፈል የወጪ ማካካሻ ክፍያ ከአሸናፊው ተጫራቹ ጋር በሚደረገው የፕሮጀክት ስምምነት የሚወሰነው ለፕሮጀክቱ የሚውለው የፋይናንስ ማቅረቢያ ቀነ ገደብ ከማለፉ እና የፕሮጀክቱ ትግበራ ከመጀመሩ በፊት በፕሮጀክቱ ስምምነት እንደ ቅድመ ሁኔታ ተወስዶ ጨረታውን ባሸነፈው የግል ባለሀብት እንዲከፈል መደረግ አለበት፡፡ ይህ ግዴታ በመወዳደሪያ ሀሳብ መጠየቂያ ውስጥ በግልጽ መጠቀስ አለበት፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## የመንግስትና የግል አጋርነት ስምምነት ይዘትና አፈጻጸም

## 26. የስምምነት ጊዜ

1. በአዋጁ አንቀጽ 45 መሰረት በመንግስትና በግል አጋርነት የሚካሄድ ፕሮጀክት የቆይታ ጊዜ እንደፕሮጀክቱ ዓይነትና ባህሪ የሚወሰን ሆኖ ከሃያ እስከ ሠላሳ ዓመት ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የፕሮጀክቱ ልዩ ሁኔታ የሚጠይቅ ሲሆን ከሃያ ዓመት በታች የሚቆይ የፕሮጀክት ስምምነት ሊደረግ ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ የተመለከተው የፕሮጀክት የቆይታ ጊዜ ሲወሰን የፕሮጀክቱን ሀብት የአገልግሎት ዘመን፣ፕሮጀክቱን በቀጣይነት ለማስኬድ የሚያስችል የፋይናንስ አቅርቦት መኖሩን እንዲሁም በአለም አቀፍ የገበያ ተሞክሮ ለተመሳሳይ ፕሮጀክቶች የሚሰጠው የቆይታ ጊዜ ከግምት ሊወሰድ ይገባል፡፡



የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር የሪከርድ አስተዳደር

## 27. የፕሮጀክት ሀብቶችን ስለማስተላለፍ

የፕሮጀክት ስምምነት ስምምነቱ ከውል ጊዜው አስቀድሞ ሲቋረጥ ወይም የስምምነት ጊዜው ሲጠናቀቅ የፕሮጀክቱ ሀብቶች ወደ ተዋዋይ ባለስልጣን ወይም ሌላ የመንግስት ተቋም የሚተላለፍበትን ሁኔታ ሊወስን ይችላል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ የፕሮጀክት ስምምነቱ ተዋዋይ ባለስልጣኑ ወይም ሌላ የመንግስት ተቋም የፕሮጀክቱ ሀብቶች በአገልግሎት ምክንያት የሚከተል እርጅናን ከግምት ውስጥ በማስገባት የፕሮጀክቱ ሀብቶች በጥሩ ሁኔታ የሚተላለፉበትን አኳኃን የሚያረጋግጥበትን መንገድ መወሰን ይኖርበታል።

## 28. የፕሮጀክት ስምምነት ስለማቋረጥ

የፕሮጀክት ስምምነት የስምምነቱ ፍሬ ነገር መጣስ፣ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር መፈጠር፣ የክፍያ ግዴታን ያለመወጣት ወይም በፕሮጀክት ስምምነቱ የሚወሰኑ ሌሎች እንደአግባብነቱ ፕሮጀክቱን ሊያቋርጡ የሚችሉ ወይም እንዲቋረጥ የሚያስገድዱ ሁኔታዎችን ሊወስን ይገባል።

# ምዕራፍ አስር
# የመንግስትና የግል አጋርነት የስነ-ምግባር ደንቦች

## 29. ስነ-ምግባር

1. በመንግስትና የግል አጋርነት የተሰማሩ ሠራተኞች የሚከተሉትን የስነ ምግባር መርሆዎች ተከትለው ተግባራቸውን ያከናውናሉ፡-

ሀ/ የተፈጠረ ወይም ሊፈጠር የሚችል የጥቅም ግጭትን የማሳወቅ እና ራስን ከሂደቱ የማግለል፤

ለ/ ለዕጩ ተወዳዳሪና ፕሮጀክት ፈፃሚ የግል ባለሀብቶች እኩል የመወዳደርና የመፈጸም እድል መስጠት፤

ሐ/ በስራ አጋጣሚ ያወቃቸውን የመግአ ፕሮጀክቱን፣የተወዳዳሪ ወይም የፕሮጀክት ፈፃሚ የግል ባለሀብቱን መረጃዎች በሚስጥር መጠበቅ፤

መ/ ከዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ፕሮጀክት ፈፃሚ የግል ባለሀብት የሚቀርብን የገንዘብ ዋጋ ያለውን ስጦታ ፣ አገልግሎት ወይም የቅጥር ዕድል አለመቀበል፤

ሠ/ በስራ ሂደት ያወቃቸውን ሊፈጠሩ የታሰቡ ወይም የተፈጠሩ የሙስና ተግባራትን ለሕግ አስፈጻሚ አካላት የማሳወቅ እና ብልሹ አሰራርን ለመዋጋት የሚደረገውን ጥረት ማገዝ፤

ረ/ ለህዝብ ሀብትና ንብረት ተቆርቋሪ መሆን።



የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት

2. ማንኛውም ተወዳዳሪ የግል ባለሀብት የመንግስትና የግል ባለሀብት መረጣ እና አፈጻጸም ሊያዛባ ከሚችል ከማንኛውም ተግባር መቆጠብ አለበት፡፡ ስለሆነም፡-

ሀ/ የመንግስት መስሪያ ቤቱን ኃላፊ ወይም ሰራተኛ ተግባር ወይም ውሳኔ ለማዛባት ወይም ከግል ባለሀብቱ መረጣ እና የፕሮጀክት አፈጻጸሙ ጋር በተያያዘ መስሪያ ቤቱ ሊከተለው የሚገባውን አሰራር ለማስለወጥ በመደለያ መልክ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ማናቸውንም ዓይነት ስጦታ አለመስጠት ወይም ስጦታ ለመስጠት ቃል አለመግባት ወይም ሌላ ማናቸውንም የገንዘብ ዋጋ ያለውን ነገር ወይም አገልግሎት አለመስጠት፤

ለ/ የመግአ ፕሮጀክት የግል ባለሀብት መረጣ ወይም አፈጻጸምን ለማዛባት በማሰብ የሀሰት ማስረጃ አለማቅረብ ወይም መግለጽ የነበረበትን መረጃ አለመደበቅ፤

ሐ/ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ ከሌላ ዕጩ ተወዳዳሪ ጋር በመመሳጠር የሀሰት ውድድር አለማድረግ፤

መ/ በስራ ሂደት ያወቃቸውን ሊፈጠሩ የታሰቡ ወይም የተፈጠሩ የሙስና ተግባራትን ለሕግ አስፈጻሚ አካላት የማሳወቅ እና ብልሹ አሰራርን ለመዋጋት የሚደረገውን ጥረት የማገዝ፤

ግዴታ አለበት፡፡

## ምዕራፍ አስራ አንድ
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 30. ቅሬታዎች

1. የግል ባለሀብት ሲመረጥ በተከናወነው ወይም ሳይከናወን የቀረው ተግባር የመግአ አዋጅን እና ይህንን መመሪያ ይጥሳል ብሎ የሚያምን ተወዳዳሪ የግል ባለሀብት ለመግአ ዳይሬክተር ጄኔራል ወይም በደረጃ ለቦርድ አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንድ (1) በተደነገገው መሰረት አቤቱታ ሊቀርብባቸው አይችልም፡-

ሀ/ በመግአ አዋጅ በተደነገገው መሰረት የሚከናወን የግል ባለሀብት የመምረጫ ዘዴዎች፤

ለ/ በመግአ አዋጅ መሰረት ጨረታን ወይም የመወዳደሪያ ሀሳብን ውድቅ ማድረግ፤

3. ተዋዋዩ ባለስልጣን በጨረታው ከተመረጠው የግል ባለሀብት ጋር የፕሮጀክት ስምምነት ከፈረመ በኋላ ሂደቱ ከዚህ ደረጃ ላይ እስከሚደርስ ድረስ በመግአ



የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት

ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ወይም በተዋዋዩ ባለስልጣን በተከናወኑ ወይም ሳይከናወኑ በቀሩ ተግባራት ምክንያት የሚቀርቡ አቤቱታዎች በመግአ ዳይሬክተር ጄኔራል ወይም በቦርዱ ሊታዩ አይችሉም፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ሶስት (3) የተደነገገው ተፈጻሚ የሚሆነው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፡-

ሀ/ በዚህ መመሪያ በተወሰነው የግዜ ገደብ ውስጥ ለመግአ ዳይሬክተር ጄኔራል አቤቱታ ሳይቀርብ የፕሮጀክት ስምምነት የተፈረመ ከሆነ፤

ለ/ አቤቱታው ቀርቦ መግአ ዳይሬክተር ጄኔራል ምላሽ ከሰጠ እና አቤቱታ አቅራቢው በዚህ መመሪያ በተወሰነው የግዜ ገደብ ውስጥ የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል በሰጠው ውሳኔ ላይ ለቦርዱ አቤቱታውን ሳያቀርብ የፕሮጀክት ስምምነት የተፈረመ ከሆነ፡፡

5. በመግአ የግል ባለሀብት መረጣ ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎች በፍታሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ የተቀመጡትን የአቤቱታ ስሚ ሥነ-ሥረዓት ደንቦች በጥብቅ መከተል ሳያስፈልግ ቀለል ባለ ሥነ-ርዓት ይታያሉ፡፡

## 31. ለመግአ ዳይሬክተር ጄኔራል ስለሚቀርቡ አቤቱታዎች

1. በመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ወይም በተዋዋዩ ባለሥልጣን በተከናወነ ወይም ሳይከናወን በቀረ ተግባር ምክንያት የሚቀርብ አቤቱታ በመጀመሪያ ደረጃ መቅረብ ያለበት ለመግአ ዳይሬክተር ጄኔራል ነው፡፡

2. እጩ ተወዳዳሪ አቤቱታውን ሊያቀርብ የሚችለው ለአቤቱታው መሰረት የሆነውን ውሳኔ ካወቀበት ወይም ማወቅ ይገባው ከነበረበት ቀን ጀምሮ በአምስት (5) የስራ ቀን ጊዜ ውስጥ ይሆናል፡፡

3. አቤቱታዉ በሁለቱ ወገኖች መካከል በሚደረግ ስምምነት ካልተፈታ በስተቀር የመግአ ዳይሬክተር ጄኔራል የግል ባለሀብቱን መረጣ ሂደት በማገድ አቤቱታው ከቀረበበት ቀን አንስቶ በአስር (10) የስራ ቀናት ጊዜ ውስጥ፤ ውሳኔው የተሰጠበትን ምክንያት ወይም አቤቱታው ተቀባይነት ያገኘ ከሆነ የሚወሰደውን የማስተካከያ እርምጃ በመጥቀስ የጽሁፍ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

4. የመግአ ዳይሬክተር ጄኔራል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሶስት (3) በተወሰነው ጊዜ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም አቤቱታ አቅራቢው የመግአ ዳይሬክተር ጄኔራል በሰጠው ውሳኔ ያልረካ እንደሆነ የመግአ ዳይሬክተር ጄኔራል ውሳኔ ለአቤቱታ አቅራቢው መገለጽ ከነበረበት የመጨረሻ ቀን ወይም ውሳኔ የሰጠ ከሆነም ውሳኔው ከተገለጸለት ቀን አንስቶ በሚቆጠር ሰባት (7) የስራ ቀን ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ አቤቱታው ሊቀርብ ይችላል፡፡



የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር
የሪከርድ
አስተዳደር
አገልግሎት

## 32. ስለቦርዱ ስለሚቀርብ አቤቱታ

1. ቦርዱ አቤቱታ ሲቀርብለት ወዲያውኑ ለመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል እና/ወይም ለተዋዋዩ ባለሥልጣን አቤቱታ የቀረበ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ በጽህፈት ቤቱ በኩል ይልካል። የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ወይም ተዋዋዩ ባለሥልጣን ቦርዱ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ በጉዳዩ ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ቀጣይ እንቅስቃሴ ወዲያውኑ ማቆም አለበት።

2. ቦርዱ የእጩ ተወዳዳሪውን አቤቱታ ውድቅ ካላደረገው በስተቀር፡-

   ሀ/ የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ወይም ተዋዋዩ ባለሥልጣን ሕጉን ያልጠበቀ ተግባር እንዳያከናውን እና ውሳኔ እንዳይሰጥ ሊያግድ፤

   ለ/ የግል ባለሀብቱን ከመምረጥ ወይም የፕሮጀክት ስምምነት ከመፈረም ጋር ከተያያዙ ውሳኔዎች በስተቀር የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ወይም ተዋዋዩ ባለሥልጣን ስራውን እንዲያከናውን፤

   ሐ/ የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ወይም ተዋዋዩ ባለሥልጣን ከሕግ ውጭ ያከናወነው ተግባር ወይም የሰጠው ውሳኔ በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ እንዲሆን፣

   ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል።

3. ቦርዱ በአቤቱታው ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ስለአቤቱታው ማወቅ ለሚገባቸው አካላት ማሳወቅ፣ ከነዚህም አካላት የቀረበ መረጃ እና መከራከሪያ ሀሳብ ካለ ይህንኑ መመርመር አለበት።

4. ቦርዱ አቤቱታ ከቀረበለት ቀን አንስቶ በሃያ አንድ (21) የስራ ቀናት ውስጥ ለውሳኔው መሰረት የሆኑትን ምክንያቶች እና የተወሰዱትን የመፍትሄ እርምጃዎች በመጥቀስ ውሳኔ መስጠት አለበት።

## 33. በመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ወይም በተዋዋይ ባለስልጣን ለቦርዱ ስለሚቀርብ አቤቱታ

1. በግል ባለሀብት መረጣ ሂደት የመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ወይም ተዋዋይ ባለስልጣኑ ከተወዳዳሪ ወይም ከፕሮጀክት ፈፃሚ የግል ባለሀብቱ ሕገ ወጥ ድርጊት ወይም ሕጋዊ ጥቅሜን የሚጎዳ ድርጊት ተፈጽሞብኛል ብሎ ሲያምን በጨረታ ሰነዱ ወይም በስምምነት ሰነዱ መሰረት የሚወስዳቸው እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ጉዳዩን ለቦርዱ በጽሁፍ ያቀርባል።

2. ቦርዱ ከመግአ ዳይሬክቶሬት ጄኔራል ወይም ከተዋዋዩ ባለስልጣን አቤቱታ ሲቀርብለት አቤቱታ የቀረበ መሆኑን እና የአቤቱታውን ፍሬ ሀሳብ የሚገልጽ የጽሁፍ ማስታወቂያ አቤቱታ ለቀረበበት ዕጩ ተወዳዳሪ ወይም ለፕሮጀክት ፈፃሚ የግል ባለሀብት ይልካል።

3. ቦርዱ አቤቱታውን ለመመርመር እና ውሳኔ ለመስጠት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ጉዳዩ የሚመለከታቸውን አካላት ጠርቶ ማነጋገር ወይም መረጃ መጠየቅ እና



የቦርድ አስተዳደር

ማግኘት እንዲሁም ከማንኛውም አካል የሙያ ድጋፍ መጠየቅ እና ማግኘት ይችላል፡፡

4. ቦርዱ የቀረበለትን አቤቱታ በተገቢው በመመርመር አቤቱታው በቀረበለት በሃያ አንድ (21) የስራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ አራት (4) መሰረት ቦርዱ የሚሰጠው ውሳኔ ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል፡-

ሀ/ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው ተዋዳዳሪ ወይም ፕሮጀክት ፈፃሚ የግል ባለሀብት በማንኛውም የመንግስትና የግል አጋርነት ፕሮጀክት ውድድር ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ እንዳይሳተፍ ማገድ፤

ለ/ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

ሐ/ የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ ማድረግ፤

## 34. <u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>

ሚኒስትሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 35. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከ __________ ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አብራሃም ተከስተ (ዶ/ር)**

**የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሚኒስትር**

**__________ ቀን 2010 ዓ.ም**

**<u>አዲስ አበባ</u>**